**ዘርፍ 1**
በወረዳ መስተዳደር መሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ እንዲያገኙ ማድረግ፣

**ዘርፍ 2**
የመሰረታዊ የጤና አገልግሎት አቅርቦት፣



**ዘርፍ 3**
ዜጎች በክልሎችና በወረዳዎች በጀት ላይ ያላቸውን ግንዛቤ ማስፋት፣

**ዘርፍ 4**
የህብረተሰብ ተጠያቂነት ፕሮግራም ናቸው፡፡

የከለላ ለመሰረታዊ አገልግሎቶች ፕሮጀክት ዘርፍ የሆነው የህብረተሰብ ተጠያቂነት፤ አላማው የህብረተሰብ ተጠያቂነት ማዳበሪያ መንገዶች በዜጎችና በማህበረስብ ድርጅቶች ተጠናክረው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግና የበጀት ቀመር ሂደትን ግልጽ በማድረግ ባልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በብቃት እንዲሳተፉ ማስቻል ነው፡፡ በግንቦት 1999 በኢትዮጵያ መንግስትና በአለም አቀፍ የልማት አጋሮች የተመሰረተው የኢትዮጵያ ለህዝብ ተጠያቂነት ፕሮግራም ድጋፍ የማሰባሰብ ስራ ኢትዮጵያ የምዕተ - አመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የምታደርገውን ሂደት ለመደገፍ የታቀደ አዲስ መንገድ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዜጎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማትና አገልግሎት ሰጭዎች ማህበራዊ ተጠያቂነትን በመጠቀም መሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥን ብቃትና ጥራት ያለውና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲያደርጉ ማበረታታት የሚያስችል ዘዴ ነው ማለት ያስችላል፡፡

ስለሆነም የማህበራዊ ተጠያቂነት ዓላማ ዜጎች/የዜጎች ማህበራት በየአካባቢያቸው ስለሚያገኙት መሠረታዊ አገልግሎት ድምፃቸውን የሚያሰሙበትንና የሚጠይቁበትን ግንዛቤ መፍጠርና አግባብ ያለውን ዘዴ በሙከራ መለየት ነው፡፡

በዚሁ መሠረት የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር /አልማ/ በዋና አስተባባሪነት ከአማራ ሴቶች ማህበር፣ ከግሪን ቤልት የተቀናጀ የማ/ል ድርጅት እና ከፓክት ኢትዮጲያ ጋ ር በመተባበር በክልሉ ሁለት የከተማ አስተዳደሮችና ሁለት የገጠር ወረዳዎች የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክትን ለሙከራ ተግብሯል፡፡ ሙከራው የተተገበረባቸውም በደ/ማርቆስ እና በዳንግላ ከተማ አስተዳደሮች ስድስት ቀበሌዎች ውስጥ በሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና የጤና ተቋማት ናቸው፡፡ በተመሳሳይ፣ በፋርጣ እና በመተማ ወረዳዎቸ በስድስት ቀበሌዎች የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እና ጤና አገልግሎቶች አሰጣጥ የፕሮጀክቱ አካል ነበሩ፡፡

## የህብረተሰብ አኃዝ ካርድ

የህብረተሰብ አኃዝ ካርድ ህብረተሰብ ተኮር የመቆጣጠሪያ መሳሪያ ሲሆን፣ በተለይም በአገልግሎት አሰጣጥና በተጠሪነት ላይ ያነጣጠረ፣ በአገልግሎት ሰጭና በህብረተሰብ መካከል ያለውን መስተጋብር የሚያጠቃልል



ሆኖ፣ ፈጣን አስተያየት የሚጠይቅ ፣ ለህብረተሰቡ የሚሰጠውን አገልግሎት ጥራትና ብቃት የሚመዝን ነው። ጥቅሙ ለአካባቢው ሆኖ፣ ህብረተሰቡ መስፈርት ስለሆነ፣ በተተኮረባቸው ክፍሎች በኩል የተሰበሰቡ ጥራት ያላቸው መረጃዎች ከሁሉም ባለድርሻ አካሎች (የሚያገባቸው) ተሳትፎ ጋር የድህነት ማስወገድ ስልቶችን ውጤታማነት ለመገምገም፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሻሻልና የተሻለ ቁጥጥር አበጅቶ የተዘረጋውን ዕቅድ ለመፈጸም፣ የልዩ ልዩ ባለድርሻዎችን የጠለቀ አስተሳሰብ ለመገምገም፣ ሁኔታውን ለማሻሻል ምን መደረግ እንዳለበት በአንድነት ሆኖ ለመወሰን፣ ህብረተሰቡ መለኪያ ስለሆነ ጥራት በተተኮረባቸው ክፍሎች/ቡድኖች/ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በተግባር ላይ ለማዋል የሚረዳ ዘዴ ነው።

## አሳታፊ የዕቅድና በጀት ዝግጅት

ሕብረተሰቡ በመንግስት በጀት አሰራር ላይ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖረው የሚያስችል የማህበራዊ ተጠያቂነት ማስፈጸሚያ ዘዴ ነው። በጤና እና ትምህርት አገልግሎቶች ላይ በማተኮር የአካባቢው ተፈጥሮአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን ከመለየትና ከመተንተን አንስቶ፤ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚረዳ ዓላማ በመንደፍ፣ በዚሁም መሰረት ዝርዝር ተግባራትን በመለየት፣ ዕቅድ ማዘጋጀትን እና ለዕቅድ



ተማሪዎች በትምህርት በጀት ጉዳይ ላይ ሲወያዩ

ማስፈፀሚያ በጀት ማዘጋጀትና የየአካላቱን ድርሻ፣ የስራ ሃላፊነትና የበጀት ምንጭ እስከመግለፅ ድረስ የሚሳተፍበት ሂደት ነው።

በዚህም መሠረት፣ ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት የማህበራዊ ተጠያቂነት ማሳለጫ ዘዴዎች በመጠቀም በተመረጡት የከተማ አስተዳደሮች/ወረዳዎች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች /አዋቂ ወንዶች፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ የማህበረሰቡ ተወካዮች/ ከ10-20 ሰዎች በቡድን በመሆን በየአገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ በአካል ይገኛሉ። በየአካባቢያቸው የሚያገኙትን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እና የጤና አገልግሎት ተገቢነት ይፈትሻሉ፣ የየአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ከመንግስት የትምህርትና ጤና ፖሊሲ አንፃር ይቃኛሉ። አገልግሎቶቹን ለማሻሻል የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ የመንግስትና የህብረተሰቡን አዲስ አጋርነት ከማጉላት ባሻገር፣ መንግስት ለብቻው የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ማሳካት እንደማይችልና ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው።

በዚህ አጭር ቅኝት በጥቂቱም ቢሆን የሙከራ ፕሮጀክቱን ትግበራ በዓይነ-ህሊና እንድንቃኝ ያስችለን ዘንድ በፕሮጀክቱ ተሳትፎ ከነበራቸው አንድ አባት ጋር ቆይታ አድርገናል።

## የመኝታን ምቾት የሚያውቀው ያነጠፈው ወይስ የተኛበት?

አቶ ሙሉዓባይ ታምሩ በደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር የቀበሌ 03 ነዋሪ ሲሆኑ፣ በመምህርነት ሙያ ለረጅም ጊዜ እንዳገለገሉና አሁንም በሥራ ላይ እንደሆኑ ነግረውኛል።

ስለ ከለላ ለመሠረታዊ አገልግሎቶች የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕርጀክት ምንነት፣ ዓላማና ከፕሮጀክቱ የሚጠበቁውጤቶች...ወዘተ ለማስተዋወቅየፕሮጀክቱ የክልል እና የከተማ አስተዳደሩ ባለሙያዎች እና የፕሮጀክቱ ፈፃሚ ድርጅቶች በደብረማርቆስ ከተማ ሲኒማ አዳራሽ ተገኝተናል። በወቅቱም ከቀበሌ 03 ለመጡ ነዋሪዎች ስለፕሮጀክቱ ተገቢውን ግንዛቤ አስጨብጠን፣ ጠቃሚ ውይይቶችን አድርገናል። ፕሮጀክቱ ሲተገበር የሚመሰረቱት የውይይት ቡድኖችን በማስተባበር አመቻቺ የሚሆኑ ሁለት-ሁለት ሰዎችን ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ አስመርጠን እና ሌሎችና ቀጣይ የፕሮጀክቱን ሥራዎች ገልጸን አዳራሹን ለቀን በመውጣት ላይ እንዳለን ከኋላዬ ሙሉ ጥንካሬና አጥንተ ሰፊ የሆነ እጅ ትከሻዬ ላይ አርፎ አንገቴን እንዳዞር አስገደደኝ፣ ዞርኩም።

"ሙሉ ዓባይ ታምሩ እባላለሁ" አሉኝ። "ምን ልርዳዎት?" አልኳቸው። "ና እስኪ ወዲህ?!" ብለው በአባታዊ መንፈስ ወደ አንድ ነፃ ቦታ ወሰዱኝ። እርምጃቸው ዝግ ያለ፣ጥሞናቸው ጥያቄን የሚጭር ሆኖ አገኘሁትና "ምን ሊነግሩኝ? አለያም ሊጠይቁኝ አስበው ይሆን?" ስል ከራሴ ጋር ተነጋገርኩ። ቆም እንድንል እጄን ያዝ አደረጉኝና በትኩረት ተመለከቱኝ። "ልጄ!" ብለው ጀምረው ያጫወቱኝን እንደወረደ ይኸውላችሁ።

ስታነቡትም በአስተውሎት ይሁን::

“ልጄ! እንደምታየኝ ዕድሜዬ ብዙ ነው፣ በዕድሜዬም ሦስት መንግሥታት ተፈራርቀውብኛል:: እስካሁን በኖርኩት ዕድሜዬ ውስጥ ግን እንዲህ እስከ ቀበሌ ድረስ ወርደው የሚያስተዳድሩትን ህዝብ የሚያወያይ አካል እንዲኖር ሲፈቅዱ አላስተዋልኩም:: ቅድም ለምን እንደመጣችሁ፣ ዓላማችሁ ምን እንደሆነ ተረድቼ ሳበቃ ግን አንድ የአባቶችን ተረት ልነግርህ ወደድኩኝ” አሉኝ::

“ልጄ!” አሉኝ አሁንም በድጋሚ:: “ተረቱን ከመንገሬ በፊት ግን አሁን እናንተ ይዛችሁት ከመጣችሁት የፕሮጀክት ሃሳብ አንፃር መረዳት እንዲቻልህ ልብ ብለህ አድምጠኝ !እንዳትረሳም!” ካሉኝ በኋላ ለአፍታ አሰብ አደረጉና፣ “እኔ እንደሚገባኝ መንግሥት ለህብረተሰቡ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ብዙ ናቸው::ብዙ እንደመሆናቸው መጠን ደግሞ የህብረተሰቡን ፍላጎት ሊያረኩም ላያረኩም ይችላሉ፤ አይደለም እንዴ ልጄ?” ሲሉ ጠየቁኝና ንግግራቸውን ገታ አደረጉ:: “እርግጥ ነው!” በማለት ሃሳባቸውን መጋራቴን አንገቴን ወደላይና ወደታች በመነቅነቅ አረጋገጥኩላቸው::

ይሄኔ ነው ታዲያ “አገልግሎት እናገኛለን::ነገር




ስለበጀት ሕዝብን ለማስተማር በአልማ የተሰማሩ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመራቂ የህግ ተማሪዎች